# ትንሽ ምክር ለአንድነት ፓርቲ

(ከሀብስቱ - ሲልቨር ስፕሪንግ/ሜሪላንድ)




ሁኔታው ባይፈጠር የተሻለ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ያለው አማራጭ ችግሩ ከደረሰበት ደረጃ ተንስቶ የሚሆነውን መፍትሄ ማፈላለግ ላይ ማትኮሩ የግድ መሆን ኣለበት፡፡ አባላት በተለይ አብዛኛው ደጋፊ ደግሞ ሃላፊነት በተሞላበት ንቁ ተሳትፎ ማሳየት ከምን ጊዜም በበለጠ  ይጠበቅባቸዋል፡፡ ደግሞ እንዲህ አደረጉ? ምን ኣይነቱ ሰዎች ናቸው? እንግዲህ ወያኔ ያላግጥብን? እያሉ መራገሙ የሚፈይደው ኣይኖርም፡፡ የነገሩ መነሻና ለምንስ እዚህ ደረጃ እስከሚደርስ እንደተጠበቀ ዝርዝር  ጉዳዩን በማጥናት አስቸኳይና አስማሚ መፍትሄ መድረሱ የግድ ይሆናል፡፡ እስካሁን የታዩት ምልክቶች በተለይም ባአመራሩ የተላለፉት መግለጫዎች አንድነት ከመሰለ በእውቀት፣ በእድሜና በልምድ ከዳበረ ድርጅት የሚጠበቅ አልመሰለኝም፡፡

ስሞታና ኣቤቱታ ላቀረቡት አባላት አጥጋቢና አርኪ በሆነ መልኩ ሊያስተናግድ የሚችል መድረክ ፈጥሮ አንድነቱን እስከሁን ከነበረው በበለጠ ማጠናከር እንደሚቻል ነው የሚታየኝ፡፡ ህጉ መከበር ኣለበት፤ ድርጅታዊ መዋቅር በሚፈቅደው ችግራቸው ተስተናግደዋል፤ በሚል ብቻ ለሌች አማራጭ መፍትሄዎች በር አለመስጠት ድርጅቱ ከቆመለት በጣም ግዙፍ ዓላማ አንፃር ሲታይ የሚጠቅም ኣይሆንም፡፡

በተለይም ኣብዛሃዎቹና በከፍተኛ የድርጅቱ እርከን የሚገኙት ኣመራሮች ከሚጠበቀው በላይ የአስተናጋጅነት ባህሪ ማሳየት የበለጠ ያስመሰግናቸዋል እንጂ ክብራቸውን የሚነካና የሚያንኳስስ አይሆንም፡፡ አንዳንዴም በድርጅታዊና በፓለቲካ ችግሮች አፈታት ሊሂቃን የሆኑትን የድርጅቱ ወገንቶኞች ሆኖም ኣባላት ያልሆኑ በአማካሪነትና በአደራዳሪነት እንዲገኙ መጋበዙ ጠቃሚ ሳይሆን ኣይቀርም። ምንም እንኳ መለስ ዘናዊ ገደል ግቡ ብሎ በቀጭን ትእዛዝ ቢያፈርሰውም፤ ወያኔም ቢሆን ውስጠ ድርጅት ቀውስ የሚገራበትን የቁጥጥር (ኦዲት) ኮሚሽን እንደነበረው በክፍፍሉ ወቅት ይፋ መውጣቱ ይታወቃል። አንድነት ከዚያ ውጣ ውረድ ሁሉ የኣባላትን ብሶትና ቅሬታ ሳይውል ሳያድር ምላሽ የሚሰጥበትን መድረኮችና አካላት ኣለመፍጠሩ የሚገርም ቢሆንም አሁንም ቢሆን ጊዜው ያለፈበት ኣይደለም።

ዞሮ ዞሮ ግን የአባላትና ደጋፊዎች ከዚያም ኣልፎ ህዝብ ባጠቃላይ የጎላ ተሳትፎ ካላሳየ በተወሰኑ ሰዎች ቅን ፍላጎት ብቻ መተማመን የትም የሚያደርስ ኣይሆንም። በኢትዮጵያ ድርጅቶች የእንቅስቃሴ ታሪክ ኣዘውትሮ የሚታየው በቀውስ ወቅት የኣባላት ተሳትፎ በሚጠበቀው ደረጃ የማይታይ መሆኑን ነው፡፡ ጉልበታቸውና ገንዘባቸው እንዲሁም ህይወታቸው ሁሉ ለሰጡበት ድርጅትና ዓላማ ወኔና ቁጣ በተቀላቀለበት የተበላሸውን ለማስተካከል ቁርጠኝነት ኣያሳዩም። በኢህአፓና በወያኔ እንደዚሁም በሌሎች ድርጅቶች በመደጋገም ነው ክስተቱ የታየው። በመሆኑም የኣንድነት ኣባላትና ደጋፊዎች በሚኖራቸው መንገዶች ሁሉ በመጠቀም ድርጅታቸውን መልሶ በሚያጠናክር መንገድ የነቃ ተሳትፎ ማሳየት ይገባቸዋል። እስከኣሁን እንደታወቀው ከሆነ በእነ ፕሮፌሰር መስፍን የቀረበው እረሮና ኣቤቱታ ኣስተዳደራዊ በደልና ስልጣንን በአግባብ አለመጠቀም ሲሆን ኣመራሩ በሰከነ መንፈስ ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ማመላከት ኣለበት።

እነዚህ ሰዎች ህግን አላከበሩም፤ ለዲሞክራሲ ስርዓትና ለፓርቲው ዲስፒሊን ተገዢ ኣልሆኑም፤ የሚሉ ምክንያቶችን በመደርደር ቅሬታቸው ዲስሚስ ለማድረግ መሞከር ቢያንስ ቢያንስ አደገኛ መንገድ ይሆናል። እንኳን በድርጅታቸው ምክርቤት ወረቀት መበተን ይቅርና እንደ እንግሊዙ ፓርላማ ኣስሬ ጫጫታ በማሰማት ቅሬታቸው እንዲሰማ ቢያደርጉስ ነውሩ ምን ላይ ነው? ይልቅስ መፍትሄ እንስጠው ብሎ ኣመራሩ በበጎ ቢያየው ነው የሚሻለው። የመፍትሄ እርምጃዎቹ እስከሚወሰዱም በተለይም ኣመራሩ ገንቢ ካልሆኑ መግለጫዎች መስጠት ቢቆጠብ የሚመረጥ ይሆናል።።